# በታሪክ እስረኛው መዳፍ ውስጥ

## መነሻ

አገራችን የባለ ረጅም ዘመናት ደማቅ ታሪክ ባለቤት መሆኗ ይታወቃል። ይህ እውነታ ከአገሬው የታሪክ ባለሙያ በበለጠ የውጭ አገራት ዜጎች የታሪክ ፀሐፍትና በተለያዩ ጊዚያት በተለያየ ምክንያት አገራችን የጎበኙ የታሪክ ሙሁራን ያልሆኑም ጭምር ወርቃማው ታሪካችን በማስታወሻቸው ከትበውት ለታሪክ ተመራማሪዎች ሁነኛ መረጃና ማጣቀሻ ሆነው በማገልገል ይገኛሉ።

አብዛኛውን የአገራችን ታሪክ ደማቅና ዕድሜ ልክን ቢያደምጡት ወይ ቢያነቡት ለአፍታም ቢሆን ቀልቦን ወደ ሌላ ሐሳብ እንደማይሰረቅ እሙን ነው። ይህ ባህሪ ያለው ታሪካችን እንደተጠበቀ ሆኖ ከዘመነ መሳፍንት እስከ ወታሃደራዊ ዘመኑ ያሳለፍነው ታሪክ ደግሞ የራሱን የተወሰኑ በጎ ጎኖች የነበሩት ቢሆንም አገራችን በአብዛኛው በአሉታዊ ገፅታ እንትመዘገብ ያደረጋት መሆኑ ይታወቃል።

ሁለቱም ገፅታዎች የእኛ የራሳችን ታሪኮች ናቸው። ሁለቱም የራሳችን መገለጫዎች ናቸው። ለማንም የሚሰጡ አይደሉም። ወደድንም ጠላንም የራሳችን የታሪክ ምዕራፎች መሆናቸው መቀበል ይጠበቅብናል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የምንለው ኢትዮጵያ ተብሎ በዓለም ካርታ የሚታወቀው ድንበር ውስጥ  የሚኖር በሙሉ የሚመለከት እንደሆነ አከራካሪ አይደለም። ይህንን እውነታ ከተቀበልን በየትኛውን የአገራችን አካባቢ የተመዘገበውን መልካምም ይሁን መጥፎ የታሪክ ገፅታ  የኢትዮጵያ ታሪክ ነውና የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ነው። በየጊዜው ጠበብ ያለ ግዛት ሲያስተዳድሩ የነበሩ ንጉሳዊ/መስፍናዊ ባህሪ የነበራቸው መሪዎች የኢትዮጵያ ግዛቶች አመራሮች መሆናቸው፣ ታሪካቸውም የኢትዮጵያ ታሪክ መሆኑ ወደን መቀበል ይኖርብናል፤ አማራጭ የለንምና። እንዲሁም የራሳቸውን መንግስት መስርተው ትናንሽ ግዛቶችን ሲያስተዳድሩ የነበሩ መንግስታት በኃይል በማፍረስ አንድ አገር ፈጥረው ለመምራት ያሰቡ፣ የሞከሩ ብሎም ወደ ተግባር የለወጡ መሪዎች የኢትዮጵያ መሪዎች፣ ታሪካቸው የኢትዮጵያ ታሪክ ነው።

በዚህ ከተማመንን ስለአንድ የግዛት/ንግስና ዘመን በመጥፎ ገፅታው ሲታወስ አንድን አካባቢ ብቻ /ምናልባትም የዚያ ዘመን ባለታሪክ መሪ መገኛ የሚባል/ ሆዱን የሚቆርጠው ወይም ክፉኛ የራስ ምታት የሚታመም፤ ሌላው /ምናልባትን በዚያን ዘመን የተጎዳ/ አካባቢ ላይ የሚገኝ ልቡን ቅቤ የሚጠጣ ከሆነ ሁለቱም ጎራዎች ኢትዮጵያዊነታቸው እየዘነጉ ይመስለኛል።

## የታሪክ እስር ቤት ውስጥ መዳከር

ይህን አጭር ፅሑፍ ስለ ኢትዮጵያዊያን ማሕበረሰባዊ መሰረት ለመተረክ ወይም ስነልቦና ለመተንተን ያለመ አይደለም፤ ዓላማው የኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነትና እኩልነት የማይዋጥለት ኃይል አብዮታዊውን እንዴት በታሪክ እስረኛነት መዳፍ ላይ እየጣለው መሆኑ ለማመላከት እንጂ።

በኢዮጵያ ታሪክ በህዝቦች ግንኙነት እምብዛም በመልካም ገፅታው የማይወሳው የዘመነ አጼ ሚኒልክ ታሪክ ነው። ነገር ግን የዚያ ዘመን ተጎጂ የትኛውን ብሄር ነው? የትኛውስ ተጠቃሚ ነበር?

ብዙውን ግዜ በአገሪቱ የማሃል አካባቢዎች በተለይ አርሲ አካባቢ የተፈፀመ ግፍ ጎልቶ ይወቀሳል። እውነት ነው ይህንን ድርጊት ክፉኛ ሊወገዝም ይገባል። ለኔ ግን አርሲና ሌሎች የመሀል አገር አካባቢዎች ላይ ከተፈፀመው ጥፋት በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በኩል ያደረሰው ጥፋት የከፋ ሆኖ ይታየኛል። በአርሲና ሌሎች የአገራችን አካባቢዎች

የተፈፀሙ ግፎች ዜጎቻችን ጨፍጪል። በስተሰሜን የአገራችን ክፍል ላይ የደረሰው ጥፋት ደግሞ እንደሌላው የአገራችን አካባቢ ዜጎችን ከመጨፍጨፍ በተጨማሪ የአገሪቱ ንጉሰ ነገስት ለመሆን የሰሜኑን መሪዎች ለማስወገድ ከጠላት በማበር አገራዊ ክህደት ፈፅመዋል ባይ ነኝ። ይህንንም ስልጣናቸው ለማስፋት ያደረጉት በመሆኑ ለሳቸው በወቅቱ ትክክል ነበር። በነፍጥ ግዛት የሚያስፋፋና ስልጣን ላይ ለመቆናጠጥ የሚሞክር ማንም ኃይል የሚፈፅመው ነውና ከግዜው አንፃር ሲገመገም ለስርዓታቸው ትክክል ነበር።

ከዚህ በላይ ግን ለአገራችን እስከዘላለም የማይለቅ ጠባሳ ጥለው አልፋል። በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ትግዋይ እና ኤርትራ ውስጥ የሚገኝ ትግረዋይ አንድን ህዝብ በሁለት እንዲከፈል አልመው ከመስራታቸው በላይ ኤርትራ እራሱን የቻለ አገር እንዲሆን ምክንያትም ሆነዋል። ዋናው ችግር አንድ ብሔር በሁለት አገር እንዲከፋፈል ማድረጋቸው ሳይሆን ኤርትራ እንዲገነጠል የሰሩት ስራ ፍሬ አፍርቶ አርትራን የሚያስተዳድር መንግስት ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያ ጠላት እንዲሆን ምክንያት መሆናቸው ነው፤ አንድ ህዝብ በሁለት አገራት ተከፍሎ በሰላም ከኖረ ድንበር ትርጉም የለውምና። አንድ ብሔር፣ አንድ አገር የነበረ ህዝብ ይቅርና አገራት የሚመሩ መንግስታትና ፖለቲከኞች ጤነኛ አመለካከት ካላቸው የጋራ ዕድገትና ልማት የሚያስቡ ከሆነ የተለያዩ አገራት ዜጎችም አብረው መኖር፣ ብሎም ተደጋግፈው የጋራ ዕድታቸው እውን ከማድረግ ድንበር እንደማይገድባቸው ከአውሮፓ አገራት ሕብረት ብዙ መማር ይቻላል።

ወደተነሳንበት ጉዳይ እንመለስ። ስለዘመኑ ጥፋት በስተሰሜኑና በአገሪቱ መሀል አካባቢዎች የሚታየው ስሜትና ስሞታ ግን የተለያየ ክብደት እንዳለው ይሰማኛል። ለምሳሌ በመገናኛ ብዙሓን፣ በፓርቲ ሰነዶች ወዘተ አርሲ አካባቢ የደረሰውን ክፋት/ጥፋት ክፋኛ ሲወገዝ - ይገባልም - የሰሜኑ ክፍል ለስሙም አይነሳም። ለምን እንዲህ ዓይነት ልዩነት ተፈጠረ? የሚል ግን ትልቅ ትርጉም አለው። በሰሜን በኩል ያለው ልሂቅ የሚኒልክ ዘመን ታሪክ የአገራችን ታሪክ እንጂ የተወሰነ ማሕበረሰብ ታሪክ አይደለም ብሎ ስሚያምና መጥፎውን ታሪክ ያስከተላቸው ጥፋቶች መመለስ ስለማይቻል ከታሪኩ መማር የሚገባን ነገር ቢኖር ለቀጣይ የአገራችን ጉዞ በመጥፎ አስተማሪነቱ በግብአትነት መጠቀም ነው ብሎ ስለሚያምን ነው። ይህንን አመለካከት የሚያራምድ አካል አግባብ ካልሆነ የታሪክ እስረኛነት አምልጧል ብዬም አስባሎሁ።

አርሲ ላይ በደረሰው ጥፋት በኩል ያ መጥፎ ዘመን ቢያልፍም እንዳላለፈ በማሰብ የበቀል ክፍያ ማግኘት አለበት ብሎ የሚመኝ ልሂቅ እጅ ያለበት መስሎ ይሰማኛል። ከደረሰው ጥፋት አንፃር ለምን በቀል ታሰበ ላይባል ይችላል። ነገር ግን የታሪኩ ተግባሪና ተዋናይ አሁን የለም፤ ጠባሳ የታሪክ ገፅታ ጥሎልን አልፏልና።

“አሁን ተሁኖ የያኔ የመጥፎ ድርጊት ተዋናይ/ተግባሪ/ ኃይል ቅጣት ማግኘት አለበት የሚል አመለካከት የሚያራምድ አካል ግን መነሻ ምክንያት ይኖረው ይሆን?” ብሎ ማየት ደግሞ ተገቢ ነው። እንደኔ “አዎ ምክንያት አለው” ብዬ አበክሬ እሞግታሎህ። መነሻ ምክንያቱም አንድም ከላይ እንደተጠቀሰው በአንድ አካባቢ የተፈፀመ መልካም ታሪክ የዛ ኣካባቢ ብቻ እንደሆነ፤ ያን ታሪክ ሲፈፀም የነበረ መሪም የግሉ አድርጎ የሚያይ ኃይል ስላለ ነው። ይህ ማለት ያ በመልካም ገፅታው የሚጠቀስ የታሪክ ክፍል የኢትዮጵያ ታሪክ መሆኑ ክዶ የብቻውን ለማድረግ ቋምጧል ማለት ነው፤ ፤ ሌሎቹ መንፈግ መሰረታዊ ስህተት ቢሆንም መልካም ታሪክ የግል ለማድረግ መጣር ብቻውን ከታየ ክፋቱ በስስት ብቻ ነው የሚፈረጀው። አወንታ የግል ለማድረግ መጣር ግን መልካም ዝንባሌ ነው። በጣም የሚገርመው ግን መጥፎ ክፍሉ በመጥፎ አስተማሪነቱ ሳይሆን እንደ ጀብድ አስቦ እውቅና የሚሰጥ፣ ስነ ልቦናውም እራሱ ባለቤት አድርጎ የሚሾም መሆኑ ነው። ይህንን ኃይል አለአግባብ የታሪክ እስረኛ ሆኖ እየኖረ ነው ማለት ነው።

ሁለተኛው ምክንያት የአሁኑ ትውልድ ካለፈው ትውልድ ያለው ግንኙነትና ልዩነት ያለማወቁ ነው፡፡ ካለፉት ትውልዶች ያለን ግንኙነት የታሪክ እንጂ የድርጊት ግንኙነት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ያ ትውልድ የራሱ ግዜ ሲኖር እኛ በራሳችን ጊዜ ነው እየኖርን የምንገኘው፡፡ ይህንን እውነታ መዘንጋት በስህተት የትናንት ታሪክ የብቻዬ ነው ብሎ የሚሳሳውና ትላንት ለተፈፀመ መጥፎ ድርጊት አሁን የበቀል ቅጣት ሊቀበል የሚገባ ኣካል ኣለ ብሎ የሚያስብ ሁለቱም የታሪክ እስረኞች አድርጓቸዋል፡፡

እራሱ ከትላንት ትውልድ ያለው ግንኙነትና ልዩነት መለየት ያቃተው ትውልድ የትላንት ታሪክ በታሪክነቱ ሳይሆን ባለቤት እኔ ነኝ ብሎ እራሱ በተሳሳተ የጀብደኝነት ታሪክ የሚያስር ኣካል እስካለ ድረስ የትናንት መጥፎ የታሪክ ክፍል እኔን አይመለከተኝም ለዚያ ጥፋት ደግሞ የየበቀል ቅጣት ማግኘት የሚገባው ትውልድ አለ ብሎ የሚያምን የታሪክ እስረኛ መገኘቱ ምክንያታዊ ነው፤ የጥፋቱ አድራጊ እኔ ነኝ የሚል ግራ የተጋባ ትውልድ አለና፡፡

ያለፈው መልካም ታሪክ ሌላውን የኢትዮጵያ ህዝብ እንደማይመለከተው፣ መጥፎ የታሪክ ክፍሉ ደግሞ እንደ ጀብዱ የሚያስብ ኃይል ሌላ መሰረታዊ ችግር አለበት፤ ያም በዕውቀት ያለመብሰል ነው፡፡ ገዥ መደቦችና ህዝብ መለየት አቅቶታል፡፡ ገዥ መደቦች ከህዝብ አስተዳደር ስርዓት ፍፁም የተለየ ባህሪ እንዳላቸው አልገባውም፡፡ ገዥ መደቦች የተወሰነ ቡድን /በስልጣን ላይ ያለ ቤተ ሰብ፣ አገልጋዮቻቸውና ታማኝ ባለሟሎቻቸው/ ጥቅም የሚጠብቁ እንጂ ምልአተ ህዝቡ ምናቸው አይደለም፡፡ ስለዚህ ያለፈው መጥፎ የታሪክ ክፍል እንደ ጀብዱ የግሉ አድርጎ የሚያስብ አካል እራሱ አለአግባብ የታሪክ እስረኛ ለመሆን ተዳርጓል፡፡ እራሱ ከገዥ መደቦች ማላቀቅ ያቃተው የታሪክ እስረኛ ካለ የገዥ መደቦች ተጠቂ እንደሆነ የሚያስብ የታሪክ እስረኛ መኖሩ አይገርምም፤ አስገራሚው እራሱን ከገዥ መደቦች መለየት ያቃተው እንጂ፡፡

እራሱ ከገዥ መደቦች ማላቀቅ ያቃተው የታሪክ እስረኛ ልሂቅ ቆም ብሎ መመልከት ያለበት ትልቅ ጉዳይ አለ፡፡ ገዥ መደቦች በገዥ መደብነታቸው ሳይሆን የወጡበት አካባቢ/ማሕበረሰብ ወኪሎች አድርጎ ይስላቸዋል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ እላይ እንደተጠቀሰ ሳይገባው እራሱ የዛኔ ድርጊት ፈፃሚ ሆኖ እራሱን የሸመ ልሂቅ የገዥ መደቦቹ ድርጊት የወጡበት ማሕበረሰብ ድርጊት አድርጎ ስለሚወስደው ያ ማሕበረሰብ በማይመለከተው ድርጊት ተወቃሽ እንዲሆን እያደረገው ይመስለኛል፡፡

እውነት ግን የአጼ ሚኒሊክ ስርዓት የአማራ ህዝብ ስርዓት ነበር? በምክንያት የምናምን ከሆነ፣ መልሱ አይደለም ነው፡፡ የአማራ ህዝብ የሚጠቀምባት የተለየ መሰረተ ልማት ወይም የአስተዳደር ስርዓት እንደነበረ የሚያሳይ መረጃ የለም፡፡ ይልቁንስ ገዥ መደቦቹ ሀብት መበዝበዝ የሚችሉበት አካባቢ ላይ ነበር ዓቅማቸው ያህል ሲረባረቡ የነበሩት፡፡ ኢትዮጵያ ይህቺ ሁላችን የምናቃት አገር ናት፡፡ በዘመኑ የአማራ ህዝብ ልዩ ተቃሚ ቢሆን ኖሮ ምጣኔ ሀብታዊ ዓቅም ገንብቶ ስለሚቆይ አሁን ሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች የሚኖሩበት የኑሮ ደረጃ ላይ ባልተገኘ ነበር፡፡ እውነት ነው የስርዓቱ አገልጋዮች ከላይ እስከ ታች ተጠቃሚዎች ነበሩ፡፡ ከአማራ ክልል ብቻ ሳይሆን ከመላ አገሪቱ ሀብት ሲመዘብሩ እንደነበር ማንም የማይክደው ነው፡፡ ዳሩ ግን ይህ በታሪክ የታሰረ አመለካከት እራሱን ባልሆነ መንገድ አታሎ በህዝቡ ላይ የስነ ልቦና ጨዋታ እየተጫወተ መሆኑ ሊገነዘብና ቆም ብሎ ሊያስብበት ይገባል፡፡

እላይ እንተጠቀሰው የዚህ ተፃራሪ የሆነውን የታሪክ እስረኛ ደግሞ የመጀመሪያው የታሪክ እስረኛ ልሂቅ ስህተት መድገም የለበትም፡፡ በዛ ሊሂቅና ሊሂቁ እወክለዋለሁኝ ብሎ የሚያስበው ማሕበረሰብ ግንኙነት እንደሌለ መገንዘብ ይጠበቅበታል፡፡ በድመሩ የሁለቱም ተፃራሪ አመለካከት ያላቸው ልሂቆች ዕይታ ለማንኛውም ማሕበረ ሰብ የሚጠቅም አይደለምና ጉዳዩ መለስ በለው ቢያጠኑት ፋይዳው ጥፋት እንጂ የአንድም ወገን ጥቅም የሚያስከብር እንዳልሆነ ያረጋግጣሉ፡፡

ይህ በሁለት ተፃፀራሪ ልሂቆች የሚታየው አመለካከት የሁለቱም ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሁላችንም ጉዳይ ይመስለኛል። ስለሆነም እንድንወያይበት ብሎም የጋራ መግባባት ደርሰንበት ለጋራ ቀጣይ ዕድገታችን የተመቻቸ መደላድል መፍጠር የሚጠበቅብን ይመስለኛል። በዚህ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከጊዜ ወደ ግዜ ከእውነታ የራቁ ውዥንብሮች በተለያዩ ማሕበረሰቦች የሌለ ምስል እየፈጠሩ በህዝቦች መካከል አብሮነት፣ መተማመን በጋራ ተደገግፍ ማደግ እንዳይኖር የስ ልቦና ጨዋታ እየተጫወቱ ማንንም ሳይጠቅሙ ሁላችንም እንዲያጠፉን እየተሰራባቸው ይገኛል። የስነ ልቦና ጥቃቱ መወጣት የምንችልበት መፍትሔ ደግሞ እውነታን መፈለግ ብቻ ነው። ይህ ማለት ደግሞ መጀመሪያ እራሳችን ከስሜታዊ ውግንና ወጥተን ሁሉንም በእኩል ዓይን መዳኘት ያስፈልገናል። እውነታው ላይ ከቆመን ሁሉንም ማሸነፍ እንችላለን። ቀድመን የምናሸንፈውም የራሳችን ስህተት ይሆናል።

## አዳዲስ የታሪክ እስረኞና የአብዮታዊው ፈተና

የዘመነ መሳፍንት ታሪካችን በዋናነት እራሰቸውን በሚተዳደሩ ትናንሽ ግዛቶች የተከፋፈለ እንደነረ የሚታወቅ ነው። አንዱ ሌላውን በማንበርከክ ግዛቱን ለማስፋት የሚደረጉ ጦርነቶች የነበሩ ቢሆንም እያንዳንዱ ግዛት እራሱ የቻለ ስለነበር በህዝቦች መካከል የተዛባ ግንኙነት ነበር ማለት አይቻልም። የአገራችን ህዝቦች የተዛባ ግንኙነት ነበራቸው ወይም አልነበራቸውም ማለት የሚቻለው እነዚያ ትናንሽ ግዛቶች በአንድ አገር ጥላ መተዳደር ከጀመሩ በኋላ ነው። ጤናማ ግንኙነት አለ/የለም ለማለት የሚያስችል በጋራ የምትመራበት የአስተዳደር ስርዓት፣ ፖሊሲና ሕግ ማዕቀፍ እንዲሁም የጋራ ምጣኔ ሀብት መኖር የግድ ነውና።

ትናንሽ ራስ አስተዳደር ግዛቶች በአንድ አስተዳደር ስር ያመጣው ዘመን ለአሁኑ ዘመን እራሱን የቻለ አወንታዊ ሚና ተጫውቷል። የተበታተነውን ማሕበረሰብ በመሰባሰቡ ትልቅ ምጣኔ ሃብት መገንባት የሚችል ህብረ ብሔራዊ አገር ለመገንባት የራሱ መሰረት ጥሏል። ነገር ግን በአንድ አገር ጥላ ስር ያሰባሰበን ስርዓት ግንኙነታችን ሚዛኑን ጠብቆ እንዲሄድ ከማድረግ ይልቅ የተዛባ እንዲሆን ነበር ያደረገው።

የተዛባ ግንኙነት እንድንላበስ ጠፍንጎ ይዞን የነበረውን የግዞት ዘመን ህዝቦች ባካሄዱት ሁለንተናዊ ትግል ተወግዷል። የኢዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ መስመርን መመሪያቸው አድርገው አፅድቀውታል። ይሁን እንጂ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን አሁን አሁን የታሪክ እስረኝነት አስተሳሰብ መልኩን ቀይሮ የኪራይ ሰብሳቢነት የፖለቲካ ኢኮኖሚ መሳሪያ ሆኖ ብቅ ብሏል። በማወቅም ባለማወቅም ቁጥሩ ቀላል የማይባል የኢህአዴግ ካድሬም ጭምር ይህንን መጥፎ አመለካከት እየተጠናወተው ይመስላል። በአንዱ የአገራችን አከባቢ የሚደረገው ጥፋት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጉዳት ተደርጎ እየተወሰደ አይደለም። 2007 ዓ/ም በአማራ ክልል በቅማንት ብሔረሰብ፣ የዛሬ ዓመት ጎንደር በትግራይ ተወላጆች ላይ የደረሰው ግፍ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የተለያዩ አካባቢዎችን የደረሰው ውድመት፣ አሁን ደግሞ በኦሚያና የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች እየደረሰ ያለ ጥፋት ፈፃሚው ማን ይሁን ማንም ሁሉም ሊያወግዘው የሚገባ ሆኖ ሳለ እንደ ኢትዮጵያዊ አንድነታችን የሚቆረቁራቸው አካላት ጥቂት ሆነው ይታያሉ። መሰል ጥፋት የሚያወግዙትም አንዴ አሸከር ሌላ ግዜ ሌላ የማይገባቸው ስያሜ ሲሰጣቸው ይታያል። የኢህአዴግ ካድሬም ቢሆን ብዙውን ግዜ ከነዚህ ጥፋቶች በስተጀርባ ያለ ፍላጎት በመተንተን ተገቢውን አቋም መውሰድ ሲገባው የእኔ ከሚለው ክልል/አካባቢ ብቻ የተቃኘ አተያይ ሲያራምድ ይስተዋላል። በሌላው የሚደርሰው ጥፋት ምንም እንደማያገባው እያሰበ ስለመሆኑ ሁኔታውን ከመቃወም ዝምታ መምረጡ ማሳያ ነው።

የአብዮታዊነት አንዱ ባህሪ እኮ ተራማጅ አስተሳሰብ ነው። ተራማጅ አስተሳሰብ ለልማት የሚተጋ እንጂ ጥፋትን የሚሸከም ትከሻ የለውም። ለአንድነትና የጋራ ዕድገት ይቆማል። ኦሮሚያ ወይም የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች ላይ የሚደርሰው የህይወት መጥፋትና የሀብት ብክነት የትግራይ፣ የአማራ፣ የአፋር፣ የጋምቤላ፣ የቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣

የደቡብ ብሔርና ብሔረሰቦች ህይወትና ሀብትና ውድመት መሆኑ መገንዘብ ይኖርበታል። እንዲህ ካልታሰበ ስለኢትዮጵያ አንድነት ለማውራት ሞራሉ ከዬት ይመጣል? ስለዚህ ኢህአዴግ የካድሬውን አብዮታዊነት በመፈተሽ የእስካሁኑ ያልተገባ የታሪክ እስረኝነት በሌላ አቅጣጫ ዘፈር አውጥቶ ለጥፋት እንዳይዳርገን ፈጥኖ ፈር ማስያዝ ይገባል።

*2010 ዓ/ም አገራችን የተጋረጧት ፈተናዎች ሙሉ በሙሉ የሚፈቱበና በሙሉ ዓቅም ወደ ልማት ምህዋር የምትመለስበት ይሁንልን !*

*ሰላም ተመኘሁ።*

*መልካም ነኝ ከአዲስ አበባ*

*09-29-17*